## በውጭ አገር የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በውጭ ምንዛሪ የሚከፍቱት ተቀማጭ ሂሣብ

- ይህ ሂሣብ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የውጭ ምንዛሪ ተቀማጭ ሂሣብ አገራቸው በሚገኝ ባንክ እንዲከፍቱ ያግዛል፡፡
- ይህን ሂሣብ ግለሰቦች እንዲሁም ዋና መስሪያ ቤታቸው ውጭ ሀገር የሚገኝ ድርጅቶች መክፈት ይችላሉ፡፡
- ሂሣቡን መክፈት የሚቻለው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የውጭ አገር ገንዘቦች ብቻ ነው፡፡
    - የአሜሪካን ዶላር
    - የእንግሊዝ ፓውንድ
    - ዩሮ
- ወደተከፈተው ሂሣብ በካናዳ ዶላር፣ በጃፓን የን፣ በሳውዲ ሪያል፣ በአውስትራሊያ ዶላር እና በዩናይትድ ዓረብ ኤሚሬትስ ድርሃም የተላከ ገንዘብ ከላይ ከተጠቀሱት ከሶስቱ የውጭ ምንዛሪ ገንዘቦች ወደ አንዱ ተመንዝሮ ተቀማጭ ይሆናል፡፡

### የተቀማጭ ሂሣብ ዓይነቶች

### 1. አስቀድሞ ለሚወሰን የጊዜ ገደብ ተቀማጭ የሚሆን ሂሣብ

- ለተወሰነ የጊዜ ገደብ የሚቀመጥና ወለድ የሚከፈልበት ሂሳብ ነው፡፡
- አነስተኛው የጊዜ ገደብ ሶስት ወራት ነው፡፡
- ሒሳቡን ለመክፈት የሚያስፈልገው ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን 5,000 የአሜሪካን ዶላር ወይንም ከላይ ለተጠቀሱት የውጭ ገንዘቦች ተመጣጣኝ እየተሰላ ይሆናል፡፡
- ወለድ ተከፋይ የሚሆነው ተቀማጭ ሂሳቡ ለተከፈተበት አነስተኛ የጊዜ መጠን ተቀምጦ ሲቆይ ብቻ ነው፡፡
- ከዚህ ሂሣብ የሚገኘው የወለድ ገቢ ከግብር ነፃ ነው፡፡
- ሒሳቡ ከተከፈተና ገንዘቡ ከተላለፈ በኋላ ባንኩ ለደንበኛው ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይሰጣል፡፡

### 2. ተንቀሳቃሽ ሂሣብ

- በማንኛውም ወቅት ቼክ በመፃፍ ከዚህ ሂሣብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ ይቻላል፡፡
- ይህንን ሂሣብ ለመክፈት የሚያስፈልገው አነስተኛው የተቀማጭ ገንዘብ መጠን 100 የአሜሪካን ዶላር ወይም የዚህ ተመጣጣኝ በሆነ ዩሮ እና የእንግሊዝ ፓውንድ ሲሆን ከፍተኛው የገንዘብ መጠን ደግሞ 50,000 የአሜሪካን ዶላር ወይም የእርሱ ተመጣጣኝ ዩሮ እና የእንግሊዝ ፓውንድ ነው፡፡
- በዚህ ሂሣብ ላይ ለአስቀማጩ ወለድ አይከፈልም፡፡
- ከዚህ ሂሣብ ላይ በውጭ ምንዛሪ ወጪ ማድረግ የሚቻለው የሂሳቡ ባለቤት ከኢትዮጵያ ውጭ እንደሚኖሩ የሚያረጋግጡ ሰነዶች ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

### 3. ወደ ውጭ አገር ሂሣብ ወይም ገንዘብ መዘዋወር የማይችል በብር የሚቀመጥ ሂሣብ

- ይህ ሂሣብ የተላከው የውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ ገንዘብ ተቀይሮ በብር የሚቀመጥና የአገር ውስጥ ክፍያዎችን ለመፈፀም የሚያገለግል ነው፡፡
- ወደዚህ ሂሣብ ተቀማጭ የሚሆን ገንዘብ በዕለቱ ባለው የውጭ ምንዛሪ መጠን ተሠልቶ ወደ ብር ተቀይሮ ተቀማጭ ይሆናል፡፡
- በዚህ ሂሣብ ላይ ለአስቀማጩ የሚከፈለው የወለድ መጠን ከመደበኛው የተቀማጭ ሂሣብ የወለድ መጠን እጥፍ ይሆናል፡፡ (በአሁን ጊዜ ስራ ላይ ያለው የወለድ መጠን 10% ነው)

- በማንኛውም ወቅት ቼክ በመፃፍ ከዚህ ሂሣብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ ይቻላል፡፡
- ከዚህ ሂሣብ በውጭ ምንዛሪ ገንዘብ ማውጣት አይቻልም፡፡

### የብቁነት መስፈርቶች

የዚህ ሂሣብ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉት

- በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣
- በውጭ አገር የሚኖሩ በትውልድ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች፣
- ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው ነገር ግን በሥራ ምክንያት በውጭ አገር ከአንድ ዓመት በላይ የኖሩ እንዲሁም በውጭ ሀገር ከአንድ አመት በላይ ለሚያቆይ ሥራ የሚጓዙና ለዚህም በቂ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡

### የሂሣቡ አከፋፈት ሁኔታ

- ከላይ የተጠቀሱትን የሚያሟሉ በውጭ የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በግንባር ቀርበው አልያም በፖስታ ቤት በኩል ይህንን ሂሣብ መክፈት ይችላሉ፡፡
- በግንባር መቅረብ የማይችሉና ይህንን ሂሣብ መክፈት የሚፈልጉ አመልካቾች ማንነታቸውን ለማረጋገጥ በያሉበት አገራት ባሉ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በኩል ሒሳቡን መክፈት ይችላሉ፡፡
- የውክልና ስልጣን የተሰጣቸው ግለሰቦች በወካያቸው ስም ይህንን ሂሣብ መክፈት አይችሉም፡፡ ነገር ግን የውክልና ስልጣን ማስረጃቸው ላይ በግልጽ የተቀመጠ ከሆነ ይህንን ሂሣብ በወካያቸው ስም ማንቀሳቀስ ይችላሉ፡፡

### ሂሣቡ የሚዘጋበት ሁኔታዎች

ይህ ሂሣብ ከሚከተሉት በአንዱ ወይም ከዛ በላይ በሆኑት ምክንያቶች ሊዘጋ ይችላል

- አስቀማጩ ሂሣቡ እንዲዘጋለት ጥያቄ ሲያቀርብ ፣
- አስቀማጩ የውጭ አገር ቆይታውን አጠናቆ ወደኢትዮጵያ ሲመለስ።

### አስፈላጊ ሠነዶች

- በትክክል የተሞላ እና በሂሣብ ከፋቹ የተፈረመ የማመልከቻ ቅጽ፣
- ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የኢትዮጵያዊነት ፓስፖርትና የሚኖሩበት አገር የመኖሪያ ፍቃድ፣
- በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው የውጭ አገር ዜግነት ላላቸው ዜግነት የወሰዱበት አገር ፓስፖርትና በትውልድ ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ መታወቂያ።


የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
ሁሌም የሚተማመኑበት ባንክ

ስልክ:-251-11-515-38-45/251-11-515-66-61
ፋክስ: 251-11-552 79 71
ፖ.ሣ.ቁ. 255
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
የስዊፍት አድራሻ፡- CBETETAA
ኢ.ሜይል: cbe_swift@combanketh.et
cbediaspora@combanketh.et
ድረ ገጽ: www.combanketh.et


# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

# COMMERCIAL BANK OF ETHIOPIA



## Diaspora Account

**Deposit your Money in the Reliable Native Bank!**